# የማህበራዊ ዋስትና ኢንሹራንስ ስርዓቶች

**የስዊዘርላንድ ነዋሪዎች በማህበራዊ ኢንሹራንስ ከተለያዩ የአደጋ ስጋቶች ይጠበቃሉ። የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ለምሳሌ አንድ ሰው ሥራውን ካጣ ወይም ከታመመ ድጋፍ ይሰጣሉ።. በተጨማሪም ቤተሰቦችን እና አረጋውያንን ይደግፋሉ።.**

## መሰረታዊ መርሆዎች

የማህበራዊ ዋስትና የሚሸፈነው በስዊዘርላንድ ነዋሪዎች ነው። የአብሮነት መርህ ተግባራዊ ይሆናል፡ አብዛኛው ህዝብ መዋጮ የሚከፍል ሲሆን ግለሰቦች እና የተወሰኑ የህብረተሰቡ አባላቶች ደግሞ ድጋፍ/ድጎማ/ ያገኛሉ። ማህበራዊ ዋስትና በአብዛኛው ግዴታ ነው። ሆኖም ግን መዋጮዎቹ በቀጥታ ከሠራተኞች ደመወዝ ይቀነሳል። ነገር ግን ቀጣሪዎች፣ በግል ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች እና ስራ የሌላቸው የገንዘብ መዋጮ ያደርጋሉ።

## አገልግሎቶች

ማህበራዊ ኢንሹራንሱ በተወሰኑ የህይወት ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይደግፋል። ዕለታዊ አበል፣ ጡረታ ወይም አበል ወይም በህመም ግዜ እና በአደጋ ግዜ ወጪዎችን ይሸፍናሉ። የማህበራዊ ዋስትናዎች ኢንሹራንሶች ሁሉም በመንግስት ቁጥጥር ስር ናቸው።

## ድጋፍ ለማግኘት ምን ያስፈልጋል?

- በእርጅና ጊዜ፣ በሞት እና በአካል ጉዳት ወቅት (3ቱ ምሰሶዎች ፣ AHV/IV፣ የሙያ ጡረታ፣ የግል ጡረታ)
- በህመም ወይም በአደጋ ጊዜ (የጤና እና የአደጋ ዋስትና ኢንሹራንስ)
- በወሊድ ጊዜ (የወሊድ አበል)
- ሥራ አጥነት ሲያጋጥም (የሥራ አጥነት ዋስትና)
- ልጆች ካለዎት (የቤተሰብ አበል)

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/soziale-sicherheit/sozialversicherungssystem